# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# የአካባቢ ጥበቃ እና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን

## የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አፈጻጸም

## መመሪያ ቁጥር አንድ/፩/

መጋቢት/2013

**አዲስ አበባ**

## መግቢያ

የአዲስ አበበ ከተማ የሀገራችን ዋና መዲና፤ የአፍሪካ መቀመጫ፤ የአለም አቀፍ ድርጅቶችና ኤምባሲዎች የሚገኙበት ከተማ እንደመሆኗ መጠን በዓለም ላይ የከተሞች እድገት በመጠንም ሆነ በቁጥር እጅግ ፈጣን እየሆነ መጥቷል፡፡ የኢኮኖሚና የማህበራዊ አውታሮች እድገትም በአብዛኛው በከተሞች አካባቢ ጎልቶና ተከማችቶ ይታያል፡፡ የከተሞች የህዝብ ብዛት እድገትም ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍጥነት እየጨመረ ይገኛል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የመኖሪያ ቤት እጥረትና የአካባቢ ብክለት በከተሞች አካባቢ እጅግ የከፋ ችግር ሆኖ ይገኛል፡፡

Comment [u1]: ከዋናዉ ሀሳብ ጋር አብሮ አይሄድም

በአገራችን ከሚከናወኑ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ተቋሞች መካከል አብዛኞቹ በከተሞች አካባቢ የሚገኙ ናቸው፡፡

በተለይም አዲስ አበባ እንድታድግ እድል ከፈጠሩላት በርካታ ምክንያቶች በመነሳት ሰፊ የማህበራዊና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚደረግባት ከተማ በመሆኗ በአገሪቱ ውስጥ ከሚከናወኑት የልማት ስራዎች አብዛኞቹ በከተማዋ ይገኛሉ፡፡ እነዚህን በከተማዋ በመስፋፋት ላይ የሚገኙ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ተከትሎ በርካታ ህዝብ ከገጠር ወደ ከተማ እየፈለሰ የሚኖርባት እና የመኖሪያቤት እጥረት ያለባት ከተማ በመሆኗ ነዋሪዎች ደረጃዎችን ባልጠበቁና ባልተሟሉ ቤቶች ተፋፍገው ይኖሩባታል፡፡ የዚህ ዓይነቱ አኗኗር ከዓለም ሙቀት መጨመር ጋር ተደምሮ ከሚያስከትለው ጫና በተጨማሪ በከተማችን ከሚከናወኑት የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች የሚመነጩ ለአካባቢ ደህንነት የማይበጁና በጤናማና ባልተበከለ የመኖር ህገ መንግስታዊ መብት የሚያቃውሱ በርካታ የአካባቢ ብክለት ችግሮች በመከሰት ላይ ይገኛሉ፡፡

Comment [u2]: መጨመቅ ቢቻል፤ ተደጋጋሚ ሀሳቦች አሉበት

በመሆኑም እነዚህን ችግሮች ከወዲሁ ለመግታት በፌዴራል መንግስት ከወጡት የአካባቢ ህጎች በተጨማሪ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ከከተማዋ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት በአካባቢ ደህንነት ላይ ያተኮሩ በርካታ ደንቦችን አውጥቷል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 25/2000 ነው፡፡ ይህን ደንብ ለመተግበር ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህን የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አፈጻጸም መመሪያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርእስ**

   ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ እና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አፈጻጸም መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ትርጓሜ

   " የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የማይሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ

   1. አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው::
   2. "ከተማ" ማለት አዲስ አበባ ነው::
   3. "ኮሚሽን" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃና አረንገጓዴ ልማት ኮሚሽን ከማዕከል እስከ ወረዳ ያለውን መዋቅር ያካተተ ነው፡፡
   4. "አካባቢ" .ማለት በመሬት፣ በከካባቢ አየር፣ በአየር ሁኔታና በአየር ንብረት፣ በውሃ በህያዋን፣ በድምጽ፣ በሽታ፣ በጣዕም፣ በማህበራዊ ጉዳዮች እና በስነውበት ሳይወሰን በተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች ወይም በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በጠቅላላ ያሉበት ቦታ፣ እንዲሁም መጠናቸው ወይም ሁኔታቸው፣ የሰው ወይም የሌሎች ህያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ መስተጋብሮቻቸው ድምር ነው::
   5. "በካይ" ማለት ፈሳሽ፣ ጠጣር ወይም ጋዝ የሆነ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ

      ሀ. ያረፈበትን የአካባቢ ክፍል ጥራት በመለወጥ ጠቀሜታ የመስጠት አቅሙን የሚያጓድል ወይም

      ለ. በሰው ጤና ወይም በሌሎች ህያዋን ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ሊያደርስ የሚችል መርዝን፣ ክርፋትን፣ ጨረርን፣ ድምጽን፣

ንዝረትን፣ ሙቀትን ወይም ሌላ ክስተትን የሚያመነጭ ማንኛውም ነገር ነው::

6. "ቆሻሻ" ማለት ተጠቅመንበት ያለፈ ሆኖ በአካባቢ ወይም በሰው ደህንነት ወይም ጤና ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚታመን ማንኛውም ነገር ነው::
7. "ደረቅ ቆሻሻ" ፡- ማለት የማይፈለግ ተብሎ የተጣለ ማንኛውም ቆሻሻ ወይም ነፋሽ ያለሆነ ነገር ነው::
8. "አካባቢ መበከል" ማለት በውል ታስቦም ይሁን ሳይታሰብ በካይን ወደ ማንኛውም የአካባቢ ክፍል መልቀቅ ነው::
9. "አካባቢ ብክለት" ፡- ማለት በአካባቢ ትፈጥሮአዊ ሁኔታ ላይ ለውጥ በማስከተል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በህይወት፣ በግንባታዎች ወይም በሰው ልጅ ተለምዶአዊ ኑሮ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ነው::
10. "የአካባቢ ተቆጣጣሪ" ማለት በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር በደንብ ቁጥር 25/2000 አንቀጽ 12 መሰረት ኮሚሽኑ በአካባቢ ብክለት ተቆጣጣሪነት የተመደበ ሰራተኛ ነው::
11. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::
12. "የአካባቢ ደረጃ" ማለት በአካባቢ መኖር ያለበት የውሃ ጥራት፣ የአፈር ጥራት፣ የድምጽ መጠን፣ የሙቀት መጠን፣ የአየር ጥራት የመሳሰሉትን የበካይ ነገሮች ልቀት መጠንን ያጠቃልላል::
13. "**ደረጃ**" ፡- ማለት የአካባቢ የጥራት ወይም የብክለት መጠን መለኪያ መስፈርት ነው፡፡
14. "የአካባቢ ክፍል" ማለት የአካባቢ አካል የሆነ እንደ መሬት፣ ውሃ፣ አየር እና በውስጣቸው የሚይዟቸውን ህያውና ግዑዝ አካላትን ያጠቃልላል::
15. "ኬሚካል"፡ ማለት ኤለመንት ወይም ያለተቀላቀለም ይሁን የተቀላቀለ ዉህድ፣ ወይም ተቀምሞ በሰዉ የተሰራ ወይም ደግሞ ከተፈጥሮ የተገኘ ቁስ አካል ነዉ::
16. "አየር" ማለት ተፈጥሮዐዊ የሆነ የተለያዩ ጋዞች ቅልቅል ሲሆን በዚህ መመሪያ ዉስጥ ከመኖሪያ ቤት ዉጭ ያለዉ አየር በስራ ቦታ ህዝባዊ ግልጋሎት የሚሰጥበት ቦታ ያለዉ አየር ነዉ::

17. "ፍሳሽ" ፦ ማለት ተጣርቶ ወይም ሳይጣራ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ወደ አካባቢ የሚለቀቅ ቆሻሻ ዉሀ ወይም ሌላ ቆሻሻ ፈሳሽ ነዉ፡፡
18. "አደገኛ ቆሻሻ"፦ ማለት ተፈላጊነት የሌለዉ ሆኖ በአካባቢዉ ወይንም በሰዉ ደህንነት ወይም ጤና ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚታመን ማነኛዉም ነገር ነዉ፡፡
19. "አደገኛ ነገር" ፦ ማለት በሰው ጤና ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ጠጣር፣ፈሳሽ ወይም ጋዝ ወይም ተክል፣እንስሳ ወይም ረቂቅ ህዋስ ነው፡፡
20. "መልቀቅ" ማለት በዉል ታስቦም ይሁን ሳይታሰብ በካይን ወደ ማንኛዉም የከካባቢ ክፍል መጨመር ነዉ፡፡
21. አስወጋጅ ማለት በአደገኛ ቆሻሻ ማስወገድ ስራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ማለት ነው፡፡
22. አመንጪ ማለት ማንኛውም ቆሻሻን የሚያመነጭ ሰው ወይንም ድርጅት ሲሆን አመንጪው ባልታወቀበት ሁኔታ አደገኛ ቆሻሻውን በማወቅ ወይም ባለማወቅ በይዞታው ስር አድርጎ የሚገኝ ነው
23. ጉድፍ ማለት የጠርሙስ ስባሪ፣ የብረት፣ የሲጋራ፣ የፕላስቲክ ወይም የወረቀት ቁርጥራጭን፣ የጨርቅ እራፊን፣ የምግብ ትራፊን እና የአጽዋት ቅሪትን ጨምሮ የተጣለበትን ቦታ ውበት ወይንም ንጽህና የሚያሳጣ የሚጠቅምም ይሁን የማይጠቅም ማንኛውም ነገር ነው፡፡

3. ዓላማ

- የአዲስ አበባ ከተማን ከብክለት አደጋ በተሟላ ሁኔታ በመጠበቅ የኗሪዎቿን በንጽህና ባልተበከለ አካባቢ የመኖር ህገመንግስታዊ መብትን በማስከበር ከተማዋን ምቹና ተስማሚ የመኖሪያና የስራ አካባቢ ማድረግ፣
- የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ተግባርን ፍትሀዊና ተጠያቂነት ያለበት ግልጽና ቀልጣፋ አሰራርን በመከተል አስቀድሞ በመከላከል ላይ ማተኮርና ተበክሎም ሲገኝ መርህን በመከተል በካዮች ላደረሱት ብክለት ተጠያቂ በማድረግ በካዩ ያደረሰውን ጉዳት ወደ ቀድሞው ሁኔታ የሚመለስበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ አካባቢ ሊበክሉ የሚችሉ ነገሮችን በማመንጨት ወይም በማውጣት በአካባቢ ደህንነት ላይ ብክለት እና ሌሎች አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ሊያስከትሉ በሚችሉና ይችላሉ ተብለው በሚገመቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 5. የበካይ ነገሮች አያያዝና አወጋገድ ስርዓት

### 5.1 ደረቅ ቆሻሻ

ደረቅ ቆሻሻ ከሰው ወይም ከእንስሳት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚመነጭ ወይም የሚፈጠር ሲሆን አያስፈልጉም፣ አይጠቅሙም ወይም አገልግሎታቸውን ጨርሰዋል ተብለው የሚጣሉ ነገሮች ስብስብ ነው፡፡ በይዘቱም ከተለያዩ ማዘጋጃ ቤታዊ ቆሻሻዎች ጀምሮ እስከ የግብርና፣ የፋብሪካ እና የማዕድን ደረቅ ቆሻሻዎችን ያጠቃልላል፡፡

### 5.2 አደገኛ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ

አደገኛ ደረቅ ቆሻሻን በመሰብሰብ ፣በማጓጓዝ፣ በጥቅም ላይ በማዋል ወይም በማስወገድ ተግባር ላይ የሚሰማራ ማንኛውም ሰው ከሚመለከተው መ/ቤቱ በቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

5.3 ደረቅ ቆሻሻ ፡- ደረቅ ቆሻሻ የሚያካትታቸው ከመኖሪያ ቤትና ከተለያዩ ተቋማት የሚወጡ ተረፈ ምርቶች ፣ የጠርሙስ ስብርባሪ፣አገልግሎቱን የጨረሱ ጣሳ ፣ ፕላስቲክና የፕላስቲክ ከረጢቶች፣ያገለገለ የተሸከርካሪ ጎማ፣ የግንባታ እና የህንጻ ፍርስራሾች እና ሌሎቹንም ያካትታል፡፡

### ሀ/ የአደገኛ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ዝግጅት

1. በአዲስ አበባ የሚገኝ እያንዳንዱ ወረዳ ህብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ የወረዳውን የአደገኛ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ማዘጋጀትና መተግበር አለበት፣
2. እያንደንዱ ወረዳ የአደገኛ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት፣
3. እያንዳንዱ ክ/ከተማ በውስጣቸው የሚገኙትን ወረዳዎች ባዘጋጁት ዕቅድና ዘገባ ላይ ተመስርቶ አጠቃላይ የክ/ከተማውን ዕቅድና ዘገባ ማጠናቀር አለበት፡፡

### ለ/ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ

1. ማንኛውም ሰው በተቻለ መጠን አነስተኛ ቆሻሻ የሚፈጥር የአጠቃቀም ዘዴ ወይም የአመራረት ሂደት መከተል አለበት፣
2. ማንኛውም ሰው ከተፈጠረው ቆሻሻ ተመልሶ በጥቅም ላይ ሊውል የሚችለውን ለይቶ ጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ አለበት፣
3. ማንኛውም ሰው መወገድ ያለባቸውን የቆሻሻ አይነቶችን አነስተኛ ቦታ እንዲይዙ አድርጎ ማጨቅና ሊያስከትሉት የሚችሉትን ጉዳት ስነህይወታዊ ወይም ኬሚካላዊ በሆነ መንገድ ማስቀረትና ጥቅም ላይ ማዋል አለበት፣
4. ማንኛውም ሰው ከመኖሪያ ቤቱ ወይም ከድርጅቱ የሚወጣውን ቆሻሻ በአግባቡና ሳያዝረከረክ መያዝ አለበት፣
5. ማንኛውም ሰው ደረቅ ቆሻሻ ባልተፈቀዱ ቦታዎች ማለትም በየመንደሩ፣ በየመንገዱ፣ በጎርፍ መውረጃ ቱቦዎች ፣በፓርኮች፣ በአውቶቡስ ፌርማታዎች፣ በስፖርት ሜዳ፣ በወንዞችና በወንዝ ዳርቻዎች ወዘተ መጣል የለበትም፣
6. ማንኛውም ሰው ቆሻሻን ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጁ ቦታዎች ላይ ብቻ ማስወገድ አለበት፣
7. በተገቢው ሁኔታ በተሰራና በተፈቀደ የቆሻሻ ማቃጠያ ካልሆነ በስተቀር ቆሻሻን በድርጅት ውስጥ፣ በመንገድ ወይም በአደባባይ ማቃጠል ወይም እንዲቃጠል ማድረግ የተከለከለ ነው
8. ማንኛውም የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ላይ የተሰማራ ሰው ተረፈ ምርቶችን ለጤና ወይም ለአካባቢ ጎጂ ባልሆነ ሁኔታና ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ የተለየ ማጠራቀሚያ ዕቃ ማከማቸት አለበት ይህ አማራጭ ከሌለ በራሱ ሃላፊነት ወደተፈቀደ ማስወገጃ ሥፍራ ማድረስ ወይም ወደቀልዝነት የሚለወጥበትን መንገድ ማመቻቸት አለበት
9. ከግንባታና ልዩ ልዩ ሥራዎች ሂደት የሚመነጭ አፈር ፍርስራሽና ሌሎችምም መሰል አላስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ባልተፈቀዱ ቦታዎች መድፋት የተከለከለ ነው
10. ማንኛውም የቆርቆሮ ጣሳ ወይም ጠርሙስ አምራች ወይም አስመጪ ጣሳው ወይም ጠርሙሱ ከአገልግሎት በኋላ መልሶ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ዘዴ መዘርጋትና መተግበር አለበት፣

11. ውፍረቱ 0.03 ሚ.ሜ እና ከዚያ በታች የሆነ በስብሶ ከአፈር ጋር የማይዋሃድ ፕላስቲክ ማምረትም ሆነ መሸጥ የተከለከለ ነው፣

12. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ለደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃነት ከተፈቀደው ቦታ ውጭ ደረቅ ቆሻሻን መጣል ማቃጠል ወይም መቅበር አይችልም፣

13. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት አገልግሎቱን ብቃት ባለው መንገድ ማስፈፀም የሚያስችለው ፕሮግራም አውጥቶ ቆሻሻው እስኪወገድ ወይም ጥቅም ላይ እስኪውል ጥንቃቄና ጥበቃ በማድረግ ደረቅ ቆሻሻውን መሰብሰብና ማስወገድ አለበት፣

14. ማንኛውም ሰው ወይም የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በጋራ መገልገያ ገንዳዎች ውስጥ ቆሻሻን ሲያስቀምጥ ከገንዳው የመያዝ አቅም በላይ የሆነ ቆሻሻ ማምጣት የለበትም ከገንዳው ውጭ ማስቀመጥም የለበትም፣

Comment [u3]: ከደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ጋር ቢታይ፤ ከገንዳዉ የሚያነሳ ካልመጣስ ኤጄንሲው ምን ይላል ህጉ

15. በልዩ ሁኔታ መሰብሰብ የሚገባቸውን ልዩ ቆሻሻዎች ወደ ጋራ ገንዳዎች ማምጣት የተከለከለ ነው

16. ማንኛውም በተሽከርካሪ ቆሻሻ የሚያጓጉዝ ሰው ቆሻሻውን በሚገባ ሊይዝለት በሚችል ተሽከርካሪ የመጠቀምና ለአካባቢ ብክለትና ለህብረተሰቡ ጤና ችግር መንስኤ እንዳይሆንና እንዳይዝረከረክ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፣

17. ማንኛውም አደገኛ ደረቅ ቆሻሻን በመሰብሰብ በማጓጓዝ ጥቅም ላይ በማዋል ወይም በማስወገድ ተግባር ላይ የሚሰማራ ሰው/ድርጅት ከኮሚሽኑ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

18. በየደረጃው ያሉ የደረቅ ቆሻሻ አመንጪዎች፣ መንግስታዊም ሆኑ በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋም የተደራጁ ቆሻሻ አሰባሳቢዎች ቆሻሻን በአግባቡ መያዝና ማስወገድ አለባቸው

19. የደረቅ ቆሻሻ ቅብብሎሽ ጣቢያዎችና ማስወገጃ ስፍራዎች በሚዘጋጁበት ወቅት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሪፖርት ለአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን መቅረብ አለበት፡፡

### ሐ/ ስለ አደገኛ ቆሻሻዎች

1. ማንኛውም አደገኛ ቆሻሻ የሚያመነጭ ሰው ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ቦታ ከሚመለከተው አካል በሚሰጠው ፈቃድና የአወጋገድ ዘዴ ማስወገድ አለበት፡፡
2. ማንኛውም አደገኛ ቆሻሻ የሚያመነጭ ሰው /ተቋም አደገኛ ቁሶችን ወይም ቆሻሻ በተገቢ ሁኔታ በተዘጋጀና አካባቢን ወይም የአካባቢ አካላትን በማይበክል ሁኔታ ማስቀመጥ አለበት፡፡
3. አደገኛ ቆሻሻን ከሌሎች ማዘጋጃ ቤታዊ ከሆኑ ቆሻሻዎች ጋር ደባልቆ ማስወገድ የተከለከለ ነው፡፡
4. ማንኛውም ከኢንዱስትሪ የሚወገዱ ደረቅ ቆሻሻዎችን ወይም ተረፈ ምርቶችን ከአደገኛ ኬሚካል ጋር ቀላቅሎ ማስወገድ የለበትም፣
5. ማንኛውም የጤና ተቋም በሽታ አስተላላፊ ተህዋስያን ወይም ኬሚካል ጋር ንክኪ ያለውን ደረቅ ቆሻሻ ለዚሁ ተብሎ በአግባቡ በተዘጋጀ እና ደረጃዉን በጠበቀ ማቃጠያ ብቻ ማቃጠል አለበት፣
6. ማንኛውንም አደገኛ ቆሻሻ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳይዝ ቆሻሻን ማመንጨት ፣ ማስቀመጥ ፣ ማከማቸት ፣ ማጓጓዝ ፣ ማምከን ወይም ማስወገድ የተከለከለ ነው፡

## 5.2. ፍሳሽ ቆሻሻ

### 5.2.1 ከመኖሪያ ቤት የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻ

ከመኖሪያ ቤት የሚወጣ ፍሳሽ ማለት የልብስ እጣቢ፣ የመታጠቢያ ቤት እጣቢ፣ ከምግብ ማብሰያ አካባቢዎች የሚወጣ እጣቢ፣ የሽንት ቤት ፍሳሽ የመሳሰሉትን ፍሳሾች ይጨምራል፡፡ እነዚህ ፍሳሾች በሴፕቴክ ታንክ ተጠራቅመው ሴፕቲክ ታንኩ በሚሞላበት ወቅት መመጠጥና ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ባዘጋቸው የፍሳሽ ማጠሪያ ጣቢያ ሊጣራ ይገባዋል፡፡ ከላይ የተዘረዘሩትን የፍሳሽ አይነቶች ከሴፕቴክ ታንክ ውጭ በቱቦ ከግቢ ውጭ በማስወጣት ወደ መንገድና ወደ አካባቢው መልቀቅ የተከለከለ ነው፡፡ በመንገድ ዳር የተሰራው ቱቦ አገልግሎቱ የጎርፍ ውሃ ወይም የዝናብ ውሃ ማስተላለፊያ ስለሆነ ይህን ቱቦ ለሌሎች ፍሳሾች ማስተላለፊያነት መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኬሚካል ነክ ፍሳሾችን ተገቢውን የማከሚያ ዘዴ ሳይጠቀሙ ወደ ጎርፍ ማስወገጃ መልቀቅ የተከለከለ ነው፡፡

Comment [u4]: ዉሃና ፍሳሽ ምን ህግ ይኖረዋል፤ እንዳይጣረዝ

### 5.2.2 ከኢንዱስትሪ የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻ

ከማንኛውም ኢንዱስትሪ የሚለቀቁ ፍሳሽ ቆሻሻዎች ተገቢው ህክምና ተደርጎላቸው አካባቢ ሊሸከመው የሚችለው ደረጃ ላይ ሳይደርሱ በአቅራቢያ ወደሚገኘው የፍሳሽ ማስተላለፊያ ቱቦ ወይም ወደ ማንኛውም የአካባቢ አካላት መልቀቅ የተከለከለ ነው፡፡ ከቆዳ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ፣ ከቀለም ፋብሪካዎች፣ ከዘይት ፋብሪካዎች፣ ከፓስታ ፋብሪካዎች፣ ከሀጻናት ምግብ ቀማሚ ፋብሪካዎች፣ ከጎማ ፋብሪካዎች፣ ከስጋ ማቀነባበሪያዎች፣ ከጨርቃጨርቅ፣ ከፕላስቲክ፣ ከመድኃኒት ፋብሪካዎችና ከመሳሰሉትና ሌሎች የተለያዩ ፋብሪካዎችን የሚወጡ ፍሳሾ ቆሻሻዎች የፍሳሾቹ ዓይነት እንደ ፋብሪካው ዓይነት የተለያየ ስለሆነና የወጣውም ደረጃ በዚሁ መሰረት ስለሆነ በደረጃው በሰፈረው መስፈርት መሰረት መድረስ የሚገባቸው ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት መለቀቅ የለባቸውም፡፡

### 5.2.3 ከጤና ተቋማት የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻ

የጤና ተቋማት ሆስፒታሎችን፣ የጤና ጣቢያዎችን፣ ከፍተኛና መካከለኛ ክሊኒኮችንና የጤና ኮሌጆችን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ከነዚህ ተቋማት የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻዎች በአብዛኛው በሽታ አስተላላፊ ህዋሳትን ተሸካሚ እንዲሁም የተለያዩ በካይ ኬሚካሎችን የያዙ ስለሚሆኑ በተገቢው መንገድ ሳይታከሙ ወደ አካባቢ መለቀቅ የለባቸውም፡፡

### 5.2.4 ከነዳጅ ማደያዎችና ከጋራዦች የሚወጡ ፍሳሽ ቆሻሻዎች

ከላይ ከተጠቀሱት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚፈጠሩ ፍሳሽ ቆሻሻዎች በውስጣቸው የተቃጠለ ዘይት ግሪስ እና ሌሎች ኬሚካሎችን የያዙ ስለሆኑ በጥንቃቄ ሊያዙ የሚገባቸውና እነዚህ በካይ ነገሮች ከውሃው ሳይለዩ ወደ አካባቢ መልቀቅ በህግ የተከለከለ ነው፡፡ የመኪና ማጠቢያ ፍሳሽ ሳይጣራ ወደ ማንኛውም የአካባቢ ክፍል መልቀቅ ክልክል ነው፡፡ ከነዚህ አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚወገደውን የተቃጠለ ዘይት በተመለከተ በመሬት ላይ መድፋት ፈጽሞ የተከለከለ ሲሆን የተቃጠለ ዘይት ክዳን ባለው ፕላስቲክ ማጠራቀምና መያዝ አለበት፡፡ ምግብና መጠጥ ይዞ በቆየ ፕላስቲክ ማጠራቀምና መያዝ የተከለከለ ነው፡፡ የተቃጠለ ዘይት መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል የሚቻል ስለሆነ ለመልሶ ተጠቃሚዎችም ማስረከብ የሚገባ ሲሆን መልሶ ተጠቃሚዎች አካባቢን፣ አየርንና ውሃን በማይበክል መልኩ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

### 5.2.5 ከንግድ ተቋማት የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻ

በንግዱ ህብረተሰብ አካባቢ በተለያየ ሁኔታ የሚጠራቀም ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፈሳሽ ኬሚካሎች የሚኖሩ ሲሆን የእነዚህም አያያዝ በጥንቃቄ ሊሆን ይገባል፡፡ አደገኛ የሆኑ ፈሳሽ ኬሚካሎች በፕላስቲክ መያዣ መጠራቀም የሚገባቸው ሲሆን ይህም በቀዝቃዛ ቦታ ክዳን ባለው መያዣ እንዲሁም በተዘጋጀላቸው ቀዝቃዛና በሲሚንቶ በተለሰነ ቦታ እስከሚወገዱ ድረስ አንዱ ኬሚካል ከሌላኛው በማይነካካበትና በማይቀላቀልበት መንገድ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡ ሌሎቹም ጥቅም ላይ መዋል የማይችሉና አደገኛ ያልሆኑም ኬሚካሎች ቢሆኑ በተገቢው መንገድ ተይዘው መወገድ በሚገባቸው መንገድ በባለሙያ በመታገዝ ወደ አካባቢ ደረጃ ከመጡ በኋላ ማስወገድ ይገባል፡፡ ከዚህ ውጭ ግን በመንገድ ዳር ወይም በቱቦ ውስጥ ወይም በአፈር ላይ ወይም ወደ አየር ወይም ወደ ውሃ አካላት መልቀቅ የተከለከለ ነው፡፡

## 5.3. አየር ብክለት

5.3.1. ከኢንዱስትሪ፣ ከሃይል ማመንጫ፣ ከተሽከርካሪዎች፣ ከአደገኛ ነገሮች ፣ ከአምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ከመሳሰሉት የሚመነጩ አየር የሚበክሉ የበካይ ነገሮች ብናኝ/ጭስ/ ክርፋት ወይም ሽታ መጠን በአካባቢው ከሚፈቀደው ደረጃ በላይ መሆን የለበትም

5.3.2. ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር ማንኛዉም ሰዉ ለአየር ከወጣለት የጥራት ደረጀ በላይ በካይ ነገሮች ብናኝ፣ጭስ፣ ሽታና የመሳሰሉት ነገሮች ወደ አካባቢ አየር መልቀቅ ክልክል ነዉ፡፡

5.3.3. ቆሻሻ በሚቃጠልበት ጊዜ ሌሎች በካዮች ይፈጠራሉ እነሱም ካርቦን ዳይ-ኦክሳይድ፣ ካርቦን ሞኖ-ኦክሳይድ ናይትሮጅን-ዳይኦክሳይድ የመሳሰሉት እና ብናኝ በካዮች ይፈጠራሉ ስለዚህ ቆሻሻ ሲቃጠል የሚወጣዉ ጭስ አየርን በመመረዝ ለብክለት መንስኤ ስለሚሆን ከኢንዱስትሪ፣ ከሃይል ማመንጫ፣ ከመኖርያ ቤት፣ ከአምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች እንዲሁም ቁሳቁሶች ሜዳ ላይ ማቃጠል የተከለከለ ነዉ፡፡

## 5.4. የእይታ ብክለት

5.4.1. ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር ማንኛዉም ሰዉ እይታን ከተፈቀደ የምልከታ ደረጃ በላይ በካይ ነገሮች ብናኝ፣ጭስ፣ ሽታና የመሳሰሉት ነገሮች አካባቢ መበከል፤ ጉዳት ማድረስ ክልክል ነዉ፡፡

5.4.2. በልማት ምክንያት ለህንጻ ስራ፤ለመንገድ ስራ፤ ለማስታወቂያ ስራ ተብሎ የሚቀመጥ ማንኛውም አንጸባራቂ ነገር በሰውና በካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርስ የተከለከለ ነው፡፡

# ክፍል ሦስት

## 6. የብክለት ቁጥጥር መነሻዎች

### 6.1 ጥቆማ ወይም አቤቱታ

#### 6.1.1 ጥቆማ

ሀ. ማንኛውም ሰው ማንኛውም ዓይነት የአካባቢ ብክለት መድረሱን ከአወቀ ወይም ይደርሳል ብሎ ከገመተ ለኮሚሽን መ/ቤቱ ወይም በየደረጃው ለሚገኙ የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ፅ/ቤቶች በሚያመቸው መንገድ በስልክ ወይም በአካል ቀርቦ በቃል በመንገር ወይም በሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች ጥቆማውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

ለ. ጠቋሚው በካዩ ነገር የተለቀቀበትን ወይም በካይ ነገር ሊለቀቅበት ይችላል ብሎ የገመተውን አካባቢ ክ/ከተማውን፣ ወረዳውን፣ ቀጠናዉንና የአካባቢውን ልዩ ስም ከተቻለም በካይ ነገሩን የለቀቀውን ወይም ሊለቅ ይችላል ብሎ ያሰበውን አካል ስም መግለጽ ይኖርበታል፡፡

ሐ. ጠቋሚው በሰጠው ጥቆማ የተወሰደውን የማስተካከያ እርምጃ የመጠየቅና

የማወቅ መብት አለው፡፡

መ. ጠቋሚው ለሰጠው ጥቆማ ማስረጃ እንዲያቀርብ አይገደደም

ሠ. ጠቋሚው ካልፈቀደ በስተቀር ስሙንና አድራሻውን እንዲገልጽ አይገደደም ስሙ እንዳይገለጽ ካሳወቀም የጠቋሚው ስም በሚስጥር ይያዛል፡፡

### 6.1.2 አቤቱታ

ሀ ማንኛውም ሰው በሚኖርበት ወይም በሚሰራበት ወይም በሚዝናናበት ወይም ሌሎች ማህበራዊ ተግባራትን በሚፈጽምበት ወይም በሚንቀሳቀስበት አካባቢ የደረሰ የአካባቢ ብክለት እንዲወገድለት በጋራም ሆነ በተናጠል ለኮሚሽን መ/ቤት ወይም በየደረጃው ለሚገኝ የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤት መ/ቤቶች አቤቱታ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

ለ. የአካባቢ ብክለት መድረስ አለመድረሱ ባይረጋገጥም አካባቢን ሊበክል ይችላል ተብሎ የሚገመት የበካይ ነገር ልቀት መኖሩን ከአወቀ ወይም አካባቢን ሊበክል ይችላል ተብሎ የሚገመት በካይ ነገር ሊለቀቅ ይችላል ብሎ ከገመተ አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

ሐ. በጽሁፍ የሚቀርብ አቤቱታ በካይ ነገሩ የተለቀቀበትን አካባቢ ክ/ከተማውን፣ወረዳውን፣ቀጠናውን እንዲሁም ልዩ ቦታውን ስም በካይ ነገሩ መለቀቅ የጀመረበት ጊዜ፣ የሚለቀቀውን የበካይ ነገር ዓይነት፣ የሚለቀቅበትን ወቅት፣ የሚቻል ከሆነም ብክለቱ ያደረሰውን ጉዳት በዝርዝር ማካተት አለበት፡፡

መ. አቤቱታ የሚቀርበበት ቅጽ ኮሚሽን መ/ቤቱ ያዘጋጃል ሆኖም አቤቱታ አቅራቢው በመሰለው መንገድ በጽሁፍ አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

ሠ. አቤቱታ አቅራቢው በአቤቱታው ላይ መፈረም ይኖርበታል፤

ረ. አቤቱታ አቅራቢው የአቀረበውን አቤቱታ አፈጻጸም የመከታተልና ውጤቱንም የማወቅ መብት አለው፡፡

## 6.2 በኮሚሽን መ/ቤት የብክለት ቁጥጥርና ክትትል ስርዓት መነሻነት

Comment [u5]: ካልፈረመ ብክለቱ እንዲቀጥል ይደረጋል ወይ ፤ ከመሠረታዊ የብክለት እሳቤ ጋር ቢታይ

6.2.1 በመ/ቤቱ የተመደቡ የአካባቢ ብክለት ኢንስፔክተሮች ማንኛውንም ማምረቻ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም በማንኛውም ጊዜ ከአካባቢ ብክለት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋሉ፡፡

6.2.2 በተለይም የአካባቢ ብክለት ሊያደርሱ ይችላሉ ተብለው በሚገመቱ ማምረቻ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ መደበኛ የቁጥጥርና የክትትል ፕሮግራም በማውጣት ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

6.2.3 ከላይ ከ 6.2.1 እስከ 6.2.2 በኮሚሽኑ ለስራው ተግባራዊነት የተጠቀሱት ክዋኔዎች በከተማው አስተዳደሩ ስር ለሚገኙ ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎችም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## 7. የቁጥጥርና ምርመራ ስርዓት

### 7.1. ተቆጣጣሪው የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር በሚያደርግበት ጊዜ ሊያሟላቸው የሚገቡ ሁኔታዎች

7.1.1 የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ለማድረግ ተቆጣጣሪው ሲንቀሳቀስ የአካባቢ ብክለት ተቆጣጣሪ ስለመሆኑ ከኮሚሽን መ/ቤት ወይም በየደረጃው ከሚገኝ የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ፅ/ቤቶች የተሰጠ መታወቂያ መያዝና ቁጥጥር ለሚደረግበት አካል የማሳየት ግዴታ አለበት

7.1.2 ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም ወይም ድርጅት ከሚጠቀመው ግብዓት ወይም ምርት አንጻር ልዩ ጥንቃቄ የሚፈልግ ሲሆንና ግብዓቱ በተቀመጠበት ወይም የምርት ሂደት በሚከናወንበት ስፍራ ገብቶ ቁጥጥርና ምርመራ ለማድረግ የተለዩ አልባሳት፣ ጫማና ጓንት ማድረግ አስፈላጊ ከሆነ ተቆጣጣሪው ይህንኑ አሟልቶ መገኘት ወይም ተቋሙ ወይም ድርጅቱ ያዘጋጀውን መጠቀም ይኖርበታል፡፡

7.1.3 ተቆጣጣሪው ለስራው አፈጻጸም ደህንነትና መሳካት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው የፖሊስ አባላት የሰላምና ፀጥታ ጽ/ቤት ሰራተኞችና ሌሎች

ኢጋዥ ሰራተኞችን ይዞ የቁጥጥርና ምርመራ ስራውን ሊያከናውን ይቻላል፡፡

## 7.2 ቁጥጥርና ምርመራ ስለማድረግ

7.2.1 ተቆጣጣሪው መደበኛ የቁጥጥር ፕሮግራም በማውጣት ወይም ድንገተኛ የቁጥጥር ስልት በመቀየስ የስራ ባህሪው በአካባቢ ላይ ብክለትን እንዲሁም በሰው ልጅ አኗኗር፣ ጤንነት እና ደህንነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያደርሱ ይችላሉ ተብለው በሚገመቱ ተቋማት ወይም ድርጅት ወይም ሊበከሉ ይችላሉ ተብለው በሚገመቱ የአካባቢ ክፍሎች ላይ በማንኛውም ቀንና ሰዓት ቁጥጥርና ምርመራ ያደርጋል

7.2.2 ተቆጣጣሪው ቁጥጥርና ምርመራ በሚያካሂድበት ወቅት ተቋሙ ወይም ድርጅቱ መደበኛ ስራውን በተለመደው አኳኋን ማካሄድ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ግን ቁጥጥርና ምርምራ በሚካሄድበት ወቅት ተቋሙ ወይም ድርጅቱ ስራ አቁሞ ወይም ማሽን ቀዝቅዞ ከሆነ እና የማሽኑ መነሳት ለቁጥጥሩ ስራ አስፈላጊ መሆኑን ተቆጣጣሪው ካመነበት ማሽኑ እንዲነሳ መደረግ አለበት፡፡

7.2.3 ተቆጣጣሪው ቁጥጥርና ምርመራ ካደረገ በኋላ ተቋሙ ወይም ድርጅቱ ያለበትን ሁኔታ ገምግሞ የአካባቢ ብክለት ከደረጃ በላይ እያደረሰ መሆን አለመሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ይህ ሁኔታም ለተቋሙ ወይም ለድርጅቱ በጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ከማስተካከያ ሀሳብ ጋር ይገለጽለታል፤ ቁጥጥሩ የተደረገው በአቤቱታ መነሻነት ከሆነ የዚሁ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

7.2.4 ቁጥጥርና ምርምራ በሚደረግበት ወቅት ቁጥጥር ከሚደረግበት ተቋም ወይም ድርጅት የመነጨ አካባቢን ሊበክል ወይም የአካባቢን ንጽህና ሊያጓድል የሚችል ማንኛውም ዓይነት ቆሻሻ በአካባቢ ተዘርክርኮ ወይም እየፈሰሰ ከተገኘ ወይም መጥፎ ሽታ ወይም ጭስ ወይም ብናኝ ነገር ወይም በሌላ ብክለት በተገቢው ሳይያዝ ተለቆ በተቆጣጣሪው ከታዩ በካይ ነገር ወደ አካባቢው እንደተለቀቀ ከተረጋገጠ አስፈላጊው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

### 7.3 ናሙና ለምርመራ ስለመውሰድ

7.3.1 የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር በሚደረግበት ወቅት ማንኛውም የአካባቢ ብክለት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ናሙና መውሰድ ካስፈለገ ከተቋሙ ወይም ድርጅቱ ግብዓት ወይም ምርት ወይም ውጋጅ ላይ ለምርመራ በቂ የሆነ ናሙና ተቆጣጣሪው በማንኛውም ድንገተኛ ሰዓት ያለ ክፍያ ሊወሰድ ይችላል፡፡

7.3.2 ናሙናው ሲወሰድ የተቋሙ ወይም የድርጅቱ ስራ መሪ ወይም ተወካይ መገኘት ይኖርበታል፡፡

7.3.3 በናሙና አወሳሰድ ወቅት የድርጅቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ ካልተገኙ ወይም ፈቃደኛ ካልሆኑ የተቆጣጣሪ መ/ቤቱ 3 ባለሙያዎች በጋራ የሚወስዱት ናሙና ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል አምስት

## 8. የአካባቢ ብክለትን ለማረም መወሰድ የሚገባው እርምጃ

### 8.1 የበካይ ነገሮች ልቀቱን ማስቆም

8.1.1 ማንኛውም አገልግሎት ሰጭ ተቋም ወይም የማምረቻ ድርጅት ተገቢውን የውጋጅ ልቀት ፈቃድ ሳይዝ ማንኛውንም ዓይነት በካይ ነገር ወይም የአካባቢን ጽዳትና ደህንነት ሊያጓድል የሚችል ውጋጅ ወደ የትኛውም የአካባቢ ክፍል ለቆ ከተገኘ፤

ሀ. ልቀቱን በማስጠንቀቂያ በተገለፀው የግዜ ገደብ ውስጥ እንዲያቆም ተቆጣጣሪው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

ለ. ያለ አግባብ ያከማቸውን ወይም በየቦታው አዝረክርኮ ያስቀመጠውን ደረቅም ሆነ ፍሳሽ ቆሻሻ ከላይ በተራ ቁጥር 8.1.1 ሀ መሰረት በተጠቀሰው የግዜ ገደብ ካለቀ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ በማስወገድ ለሚመለከተው መ/ቤት ሪፖርት ያደርጋል፡፡

Comment [u6]: እንደ ቆሻሻዉ ዓይነትና ብዛት ቢሆን፤ ወይንም በጋራ የሚወሰን ቢሆን

### 8.2 ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ስለመውሰድ

8.2.1 በተራ ቁጥር 8 ንዑስ ቁጥር 8.1.1 ሀ እና ለ መሰረት ካልተፈጸመ ወይም በካዩን ነገር በለቀቀው አካል ተቆጣጣሪው ሊስማማበት የሚችል አማራጭ ሀሳብ ካልቀረበ ድርጅቱ ወይም ተቋሙ እንዲታሸግ ተቆጣጣሪው የውሳኔ ሃሳብ ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

8.2.2 የኮሚሽን ወይም በስሩ ያሉ ጽ/ቤቶች የድርጅቱን ወይም የተቋሙን መታሸግ አግባብ ሆኖ ካገኘው ከአምስት ቀን እስከ ሦስት ወር ለሚደርስ ጊዜ ድርጅቱ ወይም ተቋሙ እንዲታሸግ ይወስናል፤ የኮሚሽኑ ውሳኔ ድርጅቱ ወይም ተቋሙ የሚዘጋበትን ቀንና ታሽጎ የሚቆይበትን ጊዜ በመግለፅ ለሚታሸገው ድርጅት ወይም ተቋም እንዲደርስ ይደረጋል እንደዚሁም የውሳኔው ግልባጭ ለፈቃድ ሰጪ መ/ቤቶችና ሌሎች አግባብነት ላላቸው መ/ቤቶች እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

8.2.3 ድርጅቱ ወይም ተቋሙ ከመዘጋቱ በፊት የቅድመ ዝግጅት ጊዜ እንዲኖረው እንደ ችግሩ አሳሳቢነት ከ12 ሰዓት እስከ 48 ሰዓት ጊዜ ይሰጠዋል፡፡

**Comment [u7]:** ይኼዉም በጽሑፍ እንዲደርሰዉ ይደረጋል የሚል ቢታከልበት

8.2.4 እሽጋ ገንጥሎ/ ተደብቆ/ ሲሰራ የተገኘ ድርጅት ወይም ተቋም የኮሚሽኑን ውሳኔ ባለማክበሩ ድርጅቱ ወይም ተቋሙ ለተጨማሪ ሁለት ወር ተዘግቶ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ህጋዊ እርምጃዎች ይወሰዳል፡፡

### 8.3 የተዘጋው ድርጅት ወይም ተቋም ሥራ የሚጀምርበት ሁኔታ

8.3.1 በአካባቢ ብክለት በማድረሱ ወይም ብክለት ሊያደርሱ የሚችሉ ነገሮችን ወደ አካባቢ በመልቀቁና እንዲያስተካክል በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ሣያስተካክል በመቅረቱ ምክንያት በኮሚሽኑ ውሳኔ የተዘጋ ድርጅት ወይም ተቋም የኮሚሽኑን ውሳኔ አክብሮ ድርጅቱን ወይም ተቋሙን የዘጋና የበካይ ነገሮች ልቀቱን ሊያስወግድ የሚችል ቴክኖሎጂን በመጠቀም የአመራር ማሻሻያ ካደረገና የለቀቀውን በካይ ነገር ካፀዳ በኋላ የተዘጋው ድርጅት ወይም ተቋም እንዲከፈትለት ለኮሚሽኑ ሊያመለክት ይችላል፡፡

**Comment [u8]:** የዉዴታ ግዴታ ዉል መግባትና ላደረሰዉ ጥፋት የሚቀጣበት ሁኔታ ቴት ይታያል

8.3.2 የኮሚሽኑ መ/ቤትም ማመልከቻው ሲደርሰው በማመልከቻው ላይ የተገለፁት ነገሮች በትክክል የተፈጸሙ ስለመሆናቸው ወደ ቦታው ተቆጣሪዎችን በመላክ በመስክ ሲያረጋግጥ የጊዜ ገደቡ ባያልቅም የተዘጋው ድርጅት ወይም ተቋም እንዲከፈት ውሳኔ ይሰጣል የውሳኔውም ግልባጭ ድርጅቱ ሲዘጋ ግልባጭ የተደረገላቸው መ/ቤቶች ሁሉ እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

9. ልዩ ልዩ እርምጃዎች

## 9.1. የአካባቢ ብክለት ጥፋትና ቅጣት

9.1.1 የአካባቢ ብክለት ደረጃ ከተወሰደ በኋላ ለአካባቢው ከተፈቀደለት እስታንዳርድ ወይም ደረጃ በላይ ሆኖ ከተገኘ ለአምራች ድርጅት፣ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና ለሌሎች ብክለት አመንጪ ለሆኑ አካላት አፋጣኝ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡

9.1.2. የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው አካል ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮ ለአገልግሎት ሰጭ ተቋማት 3(ሶስት ) ቀን እና ለጥቃቅን እና አነስተኛ እንዲሁም በግል በአነስተኛ ደረጃ የሚያመርቱ የማምረቻ ተቋማት 7 (ሰባት ቀን) ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ብክለቱን በማስቆም፣ ችግሩን ፈትቶ ማስጠንቀቂያ ለጻፈው ኮሚሽን መ/ቤት ወይም አካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤቶች ያስተካከለበትን መረጃ ሪፖርት በጽሁፍ እና በአካል ማቅረብ አለበት፡፡ ነገር ግን የአምራች ድርጅቶች አሳማኝ ምክንያት ካቀረቡ ጉዳዩ ለኮሚሽን መስሪያ ቤት እና አካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤቶች የበላይ ሃላፊዎች ቀርቦ በግዴታ ውል ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡

9.1.3. የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው አካል ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮ ለኢንዱስትሪዎች እና ለፋብሪካዎች በ 1 ወር ጊዜ ውስጥ ብክለቱን በማስቆም፣ ችግሩን ፈትቶ ማስጠንቀቂያ ለጻፈው ኮሚሽን መ/ቤት ወይም አካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤቶች ያስተካከለበትን መረጃ ሪፖርት በጽሁፍ እና በአካል ማቅረብ አለበት፡፡ ነገር ግን ድርጅቶቹ አሳማኝ ምክንያት ካቀረቡ ጉዳዩ ለኮሚሽን መስሪያ ቤቱ እና አካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤቶች የበላይ ሃላፊዎች ቀርቦ በግዴታ ውል ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡

9.1.3. በ9.1.1. እና 9.1.2 የተገለፀው ሳይፈፅም ቢቀር ብክለት አድራሹ አካል ላይ ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

9.1.4. የመጀመሪያ የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በድጋሚ ለሁለተኛ ጊዜ አካባቢን በክሎ ከተገኘ፣ የለጥቃቅን እና አነስተኛ እንዲሁም በግል በአነስተኛ ደረጃ የሚያመርቱ የማምረቻ ተቋማት እና አገልግሎት ሰጭ

ተቋማት በ12 ሰዓት እና ለኢንዱስትሪዎች እና ለፋብሪካዎች 48 ሰዓት ውስጥ የሚበላሸን ንብረት እንዲያወጣ(ጡ) ተደርጎ ድርጅቱ ወዲያውኑ ይታሸጋል፡፡

9.1.5. ለመጀመሪያ ጊዜ የታሸገ ተቋም ወይም ድርጅት ከ10 ቀን በላነሰና ከ3 ወር ባልበለጠ ሊከፈት ይቻላል፡፡

9.1.6. አንድ የተፈጥሮ ሰው የዚህን አዋጅ ወይም በስሩ የሚወጡትን ደንቦች በመተላለፍ ወደ አካባቢ በመልቀቅ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ከ1000 (አንድ ሺ) ብር በማያንስና ከ5000 (አምስት ሺ) ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማያንስና ከአስር አመት በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡ ጥፋቱን የፈጸመው በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ከ50000 (ሀምሳ ሺ) ብር በማያንስና ከ100000 (መቶ ሺ) ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡ የስራ ሀላፊውም ከ5(አምስት) ዓመት በማያንስና ከ10 (አስር) ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም ከ5000(አምስት ሺ) ብር በማያንስና ከ10000(አስር ሺ) ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡ አስተዳደራዊ እርምጃ የወሰደው ኮሚሽን መ/ቤት የአካባቢ ብክለት ካደረሰው ተቋም ጋር የግዴታ ውል መፈራረም አለበት፡፡ መልሶ ከበከለ ግን አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል፡፡

9.1.7. በንዑስ ቁጥር 9.1.1. እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው አገልግሎት ሰጪ እና ለጥቃቅን እና አነስተኛ እንዲሁም በግል በአነስተኛ ደረጃ የሚያመርቱ የማምረቻ ተቋማት ብክለቱን ለመጀመሪያ ጊዜ ካደረሰ ብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) እና የውዴታ ግዴታ ስምምነት ፈፅሞ እሽጋው ይነሳለታል፡፡ ለኢንዱስትሪና ትላልቅ ፋብሪካዎች ብክለቱን ለመጀመሪያ ጊዜ ካደረሰ ብር 50000 (ሀምሳ ሺህ ብር) እና የውዴታ ግዴታ ስምምነት ፈፅሞ እሽጋው ይነሳለታል፡፡

ለሁለተኛ ጊዜ ብክለት አስከትሎ ከተገኘ አገልግሎት ሰጪና ለጥቃቅን እና አነስተኛ እንዲሁም በግል በአነስተኛ ደረጃ የሚያመርቱ የማምረቻ ተቋማት ብር 25000 (ሀያአምስት ሺህ ብር) እና የውዴታ ግዴታ ስምምነት ፈፅሞ እሽጋው ይነሳለታል፡፡

**Comment [u9]:** የጊዜ ገደቡ ሲያበቃ ቢባል

**Comment [u10]:** በተቋም ደረጃ የሚወጣ በመሆኑ እንዴት ይተገበራል

**Comment [u11]:** ተመሳሳይነት አለዉ አፈጻፀም ላይ

**Comment [u12]:** ከላይኛዉ ጋር ልዩነቱ ምንድነዉ ያለበለዚያ የሚጣረዝ ይመስላል

ለኢንዱስትሪና ትላልቅ ፋብሪካዎች ብክለቱን ለሁለተኛ ጊዜ ካደረሰ ብር 100000 (መቶ ሺህ ብር) እና የውዴታ ግዴታ ስምምነት ፈፅሞ እሺጋው ይነሳለታል፡፡

ለሶስተኛ ጊዜ ከሆነ ድርጅቱም የንግድ ፍቃዱ እንዲመክን ይደረጋል፡፡

9.1.8. በንዑስ ቁጥር 9.1.1. እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ የተፈጥሮ ሰው ብክለቱን ለመጀመሪያ ጊዜ ካደረሰ ብር 1000 (አንድ ሺህ ብር) እና የውዴታ ግዴታ ስምምነት ይፈፅማል፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ከፈፀመ፣ 5000 (አምስት ሺህ ብር) ይቀጣልና ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት እንዲሄድ ይደረጋል፡፡

Comment [u13]: በጣም በካይ ለሆኑት የሚያንስ ይመስላል

Comment [u14]: ተመሳሳይነት ስላለዉ ግልጽ በሆነ መልኩ አንድ ላይ ተሰብስቦ በቀመጥ

9.2 ማንኛውም ሰዉ ድርጅቱ ወይም ተቋሙ በብክለት ምክንያት የተወሰደውን አስተዳደራዊ የማሸግ እርምጃ ውሳኔ በመተላለፍ የታሸገውን ገንጥሎ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ተደብቆ ሲሰራ የተገኘ፣ በወንጀል እንዲጠየቅ ይደርጋል፡፡

10. ከተቆጣጣሪዎች ጋር በተያያዘ ስለሚፈጸሙ ጥፋቶች

10.1. የተመደበ ተቆጣጣሪ ስራውን እንዳያከናውን ያደናቀፈ ወይም ያሰናከለ ፣ ተቆጣጣሪ በህግ መሰረት የጠየቀውን ወይም ያዘዘውን ያልፈጸመ፤ በማስመሰል ተቆጣጠሪ ነው ሊባል የሞከረ፤ ተቆጣጣሪ ወደ ማንኛውም ቦታ ወይም ቅጥር ግቢ እንዳይገባ ወይም መዛግብት እንዳይመረምር ያደናቀፈ ማንኛውም ወረቀት፤ ማህደር ወይም ሌላ ሰነድ እንዳይፈተሽ፣ እንዳይገለብጥ ወይም ለይቶ እንዳየቀዳ የከለከለ፤ ለተቆጣ|ጣሪ መረጃ የከለከለ፣ ያሳሳተ ወይም የተሳሳተ መረጃ የሰጠ ማንም ሰው ጥፋት ፈጽሟል፡፡

10.2. በዚህ አንቀጽ 10.1.መሰረት ጥፋት የፈጸመ የተፈጥሮ ሰው ጥፋተኝነቱ ሲረጋገጥ ከ3000.00ብር /ሶስት ሺህ ብር በማያንስና ከ 10000.00 /አስር ሺህ/ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል ጥፋቱን የፈጸማ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል፤ ከሆነ ደግሞ ጥፋተኝነቱ ሲረጋገጥ ከብር 10000.00 /አስር ሺህ/ በማያንስና ከብር 20000.00 /ሃያ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤የስራ ኃላፊው ከአንድ ዓመት በማያነስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም ከ5000 /አምስት ሺህ ብር በማያንስና ከ10000.00ብር/አስር ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

11. መዛግብትን በተመለከተ ስለሚፈጸሙ ጥፋቶች

11.1 አንድ ሰው በዚህ መመሪያ መሰረት በመዝገብ እንዲሰፍር የተጠየቀውን የእንቅስቃሴ፣ የምርት፣ የቆሻሻ ዓይነት፣ ባህርይ ወይም መጠን ወይም ሌላ ተፈላጊ መረጃ በተገቢው ሳይመዘግብ ከቀረ ወይም በመዝገብ የሰፈረውን ከለወጠ ከ10000.00 /ከአስር ሺህ ብር/ በማያንስና ከ20000 /ሃያ ሺህ ብር/ በማይበልጥ የገንዘብ መዋጮ ይቀጣል፡፡

**12. ንብረት ስለመዉረስና ወደነበረበት ሁኔታ ስለመመለስ**

12.1. ይህንን መመሪያ በመጣስ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ሰዉ ወይም ተቋም ላይ ከሚወሰንበት ማንኛዉም ቅጣት በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ፡-

ሀ. ለጥፋቱ ተግባር የዋለ ማንኛዉም ነገር ተወርሶ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ወይም በሌላ መንግድ እንዲወገድ፣

ለ. አካባቢዉን የማፅጃ ወይም መሳሪያዉን፣ ኬሚካሉን ወይም እቃዉን የማስወገጃ ወጪ ተከሳሹ እንዲከፍል እንደዚሁም

ሐ. ጉዳት የደረሰበትን አከባቢ ተከሳሹ በራሱ ወጪ ወደነበረበት ሁኔታ እንዲመልስ ወይም ደግሞ የማይቻል ከሆነ ተገቢ ካሳ እንዲከፍል ማዘዝ ይችላል፡፡

## ክፍል - ስድስት

13. የተቋማት ዝርዝር በየደረጃው ባለ ተቋም

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን በየደረጃው ባሉ ተቋማት ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዝርዝር

13.1. በማዕከል ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው የማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት/ድርጅቶች ዝርዝር፡፡

13.1. የእርድ አገልግሎት መስጫ (ቄራዎች
13.2. የቆዳ ፋብሪካዎች እና የቆዳ መጋዘን
13.3. የጨርቃጨርቅ ድርጅቶች
13.4. የልብስ ስፌት ፋብሪካዎች / ከ100 በላይ የሰው ኃይል ያለው/
13.5. የጋዝ ማምረቻ ፋብሪካዎች/ ከ50 በላይ የሰው ኃይል ያለው/
13.6. የቀለም ፋብሪካዎች
13.7. የለስላሳ መጠጥ ፋብሪካዎች
13.8. የአልኮል መጠጥ ፋብሪካዎች
13.9. ፎም ፋብሪካዎች
13.10. የሚስማር ፋብሪካዎች/ ከ100 በላይ የሰው ኃይል ያለው/
13.11. የቆርቆሮ ፋብሪካዎች
13.12. የወተትና የወተት ተዋፅዖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች
13.13. ሆስፒታሎች
13.14. የመድኃኒት ፋብሪካዎች
13.15. የእምነ-በረድ ፋብሪካዎች
13.16. ባለ ኮከብ ሆቴል ቤቶች (3 እና ከዚያ በላይ)
13.17. ትላልቅ የዘይት ፋብሪካዎች/ ከ50 በላይ የሰው ኃይል ያለው/
13.18. የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች /ከ30 በላይ የሰው ኃይል ያለው/
13.19. ጠርሙስና ብርጭቆ ፋብሪካዎች
13.20. ሳሙናና ዲተርጀንት ፋብሪካዎች /ከ100 በላይ የሰው ኃይል ያለው/
13.21. የአሉሚኒየምና ብረታ-ብረት ማቅለጫ ፋብሪካዎች
13.22. ክፍተኛ የምሽት ክበባት ሆኖ ባንድ ያለው/ ሆቴል፣ ባርና ሬስቶራንት፣ ባር፣ ግሮሰሪ
13.23. የኬሚካልና አደገኛ ቁሶች ንግድ እና ማምረቻ
13.24. የኤሌክትሮኒክስ መገጣጠሚያ ፋብሪካዎች /ከ10 በላይ የሰው ኃይል ያለው/
13.25. የጎማ ፋብሪካዎች
13.26. ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲ)

13.27. ማተሚያ ድርጅቶች/ከ50 በላይ የሰው ኃይል ያለው/

13.28. የቶነርና ካርቲሬጅ ማምረቻ ፋብሪካዎች

13.29. ከፍተኛ የፕላስቲክ ማምረቻ ፋብሪካዎች/ከ30 በላይ የሰው ኃይል ያለው/

13.30. ቡና ማቀነባበሪያ እና እህል ማበጠሪያና ማከማቻ/ከ15 በላይ የሰው ኃይል ያለው/

13.31. የሃይማኖት ተቋማት ክትትልና ቁጥጥር

13.32. የአስፋልት ሬንጅ መደባለቂያ እና ክሬሸር

13.33. ሌሎች ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው ፋብሪካዎች

13.2. በክፍለ-ከተማ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው የማምረቻና አገልሎት ሰጪ ተቋማት/ድርጅቶች ዝርዝር፡፡

13.2.1. ፕላስቲክ ፋብሪካዎች/ከ30 በታች የሰው ኃይል ያለው/

13.2.2. የብረታ-ብረትና ኢንጂነሪንግ/መገጣጠሚያ ቶርኖ

13.2.3. የልብስ ስፌት ፋብሪካዎች / ከ30-100 የሰው ኃይል ያለው/

13.2.4. የጋዝ ማምረቻ ፋብሪካዎች/ ከ50 በታች የሰው ኃይል ያለው/

13.2.5. የሚስማር ፋብሪካዎች/ ከ100 በታች የሰው ኃይል ያለው

13.2.6. የዘይት ፋብሪካዎች/ ከ11- 50 የሰው ኃይል ያለው

13.2.7. የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች /ከ30 በታች የሰው ኃይል ያለው/

13.2.8. ሳሙናና ዲተርጀንት ፋብሪካዎች/ከ100 በታች የሰው ኃይል ያለው/

13.2.9. የኤሌክትሮኒክስ መገጣጠሚያ ፋብሪካዎች /ከ10 በታች የሰው ኃይል ያለው/

13.2.10.ማተሚያ ድርጅቶች/ከ5- 50 የሰው ኃይል ያለው/

13.2.11. ቡና ማቀነባበሪያ እና እህል ማበጠሪያና ማከማቻ/ከ15 በታች የሰው ኃይል ያለው/

13.2.12. የዱቄት ፋብሪካዎች

13.2.13. የጣውላ መሰንጠቂያ፣

13.2.14. የእንጨት ስራ ድርጅቶች

13.2.15. የከረሜላ ፋብሪካዎች

13.2.16. ሻማ ፋብሪካዎች

13.2.17. ሰም ፋብሪካዎች

13.2.18. የመስታዎት ስራ

13.2.19. የአልሙኒየም መቁረጫ ስራ

13.2.20. የጥራጥሬና የቅባት እህል ማበጠሪያ

13.2.21. የምግብ ማደራጃ

13.2.22. የመልሶ መጠቀም ስራ ድርጅቶች(ሪሳይክለሮች)

13.2.23. የእንስሳት ገበያና መቆያ በረት

13.2.24. የዶሮ እርባታ

13.2.25. የቤት እንስሳት ማድለቢያና እርባታ

13.2.26. የንብ እርባታ

13.2.27. የትላልቅና ቀላል ተሽከርካሪዎች ጥገና ማዕከላት

13.2.29. የቅባትና ጥራጥሬ እህሎችን ማበጠሪያና ማከማቻ

13.2.30. አነስተኛና መለስተኛ የአሉሙኒየም ማቅለጫና ሞልድ ስራዎች

13.2.31. የቆዳና ፕላስቲክ ጫማ ማምረቻ

13.2.32. የሃይማኖት ተቋማት ክትትልና ቁጥጥር

13.2.33. የተሽከርካሪ መገጣጠሚያና ሰርቪስ መስጫ ማዕከላት

13.2.34. የትላልቅና ቀላል ተሽከርካሪዎች ጥገና ማዕከላት

13.2.35. ከ3 ኮከብ በታች ሆቴሎች

13.2.36. የትምህርት ተቋማት(ኮሌጆች)

13.2.37. የጤና ተቋማት (ጤና ጣቢያዎች)

13.2.38. የወርቅና ጌጣጌጥ ሥራዎች

13.2.39.የድርና ማግ ማንጣትና ማቅለ

13.2.40.ክፍተኛ የምሽት ክበባት ሆኖ ሞንታርቦ ያለው/ ሆቴል፤ ባርና ሬስቶራንት፤ ባር፤ ግሮሰሪ

13.2.41.የኮስሞቲክስ ማምረቻ

13.2.42.ጣውላና ኮምፐርሳቶ እንዲሁም ሌሌች የደን ውጤቶችን ማስመጣት፣ ማከማቸትና ማከፋፈል፡፡

13.2.43.የብረታ-ብረትና የእንጨት ስራ ማዕከላት

13.2.44.ቦሮንዳዮ ብክለት ክትትል

13.2.45.የስፖንጅ ውጤቶች ማምረት

13.3. በወረዳ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው የማምረቻና አገልሎት ሰጪ ተቋማት/ድርጅቶች ዝርዝር፡፡

13.3.1.የትምህርት ተቋማት (አንደኛ፣ ሁለተኛና መሰናዶ ት/ቤቶች)

13.3.2.የጤና ተቋማት (ክሊኒኮች)

13.3.3.ኮከብ አልባ ሆቴሎች፣ ምግብ ቤቶችና ሬስቶራንቶች

13.3.4.ወፍጮ ቤቶች

13.3.5.የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታዎች

13.3.6.ፕላስቲክ ፋብሪካዎች /ከ10 በታች የሰው ኃይል ያለው/

13.3.7.የልብስ ስፌት ፋብሪካዎች / ከ30 በታች የሰው ኃይል ያለው/

13.3.8.ሳሙናና ዲተርጀንት ፋብሪካዎች/ከ30 በታች የሰው ኃይል ያለው/

13.3.9. ማተሚያ ድርጅቶች/ከ5 በታች የሰው ኃይል ያለው/

13.3.10. ዳቦና ኬክ ማምረቻዎች

13.3.11. አነስተኛ የምግብ ማቀነባበሪያዎች

13.3.12. የዘይት ፋብሪካዎች / ከ10 በታች የሰው ኃይል ያለ

13.3.13. ፎቶ ስቱዲዮዎች

13.3.14. ግሮሰሪና ምግብ ቤቶች በስፒከር የሚሰራ

13.3.15. ጎሚስታዎች

13.3.16. የገላ መታጠቢያ ቤቶች

13.3.17. የልብስ እጥበት (ላውንደሪ) አገልግሎት ሰጪዎች

13.3.18. የቤት ውስጥ ምግብ ማቀነባበሪያዎች

13.3.19. ቪዲዮና ሙዚቃ ቤቶች

13.3.20. ቡና መቁያ፣ መፍጫ፣ ማለስለሻ፣ ማከማቻና ማከፋፈያ ቤቶች

13.3.21. የእምነ-በረድ መቁረጫ፣ ማለስለሻ፣ ማከማቻና ማከፋፈያ ቤቶች

13.3.22. የጣውላ መሰንጠቂያ፣ ማለስለሻ፣ ማከማቻና ማከፋፈያ ቤቶች

13.3.23. የመኪና እጥበትና ነዳጅ ማደያ ቁጥጥር

13.3.24. ብሎኬትና ቱቦ ማምረቻ

13.3.25. የማግኒዥየም ቦርድ ስራ

13.3.26. ጠጅና አረቄ ቤቶች

13.3.27. ድምጽ የሚያመነጩ ሱቅና ቡቲክ ቤቶች

13.3.28. ታፕሰሪ

13.3.29. ቆሎ የሚሰሩ

13.3.30. ስሚንቶ እና ጅብሰም ማከማቻ፤መጋዘን

13.3.31. የአትክልትና ፍራፍሬ መሸጫ ቦታዎች

13.3.32. የሃይማኖት ተቋማት የድምጽ ክትትልና ቁጥጥር

13.3.33. ሌሎች ባህርያቸው ተመሳሳይ የሆኑና በአካባቢ ላይ ብክለት ያላቸው ድርጅቶችና ተቋማ

**Comment [u15]:** 1.የክትትል ክፍፍሉ በሚያሰማሩት የሰዉ ሀይል ብዛት መሆኑ ምክንያቱ ቢገለጽ 2.የብክለት ዓይነት፤ የማምረቻዉ ቴክኖሎጂ ዉስብስብነት፤ የብክለት መለኪያ መሳሪያዎች መኖር፤ የባለሙያዉ ተጋላጭነት ወዘተ ቢታይ አይሻልም

## 14. የስራ ክፍፍል አተገባበሩን በተመለከተ

14.1. ከላይ በክፍል ስድስት በማዕከል፣ በክ/ከተማ እና በወረዳ የተደረገው የስራ ክፍፍል እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን በሚመለከተው አካል ሳይፈታ ቀርቶ በአቤቱታ ሆነ በጥቆማ ጉዳዩ ወደ ሚቀጥለው መዋቅር ከመጣ ያለምንም ክልከላ ማእከል ወደ ክ/ከተማ እና ወረዳ እንዲሁም ክ/ከተማ ወደ ወረዳ ወርዶ ችግሩን ይፈታል፡፡

14.2. ወረዳ ላይ የተሟላ ባለሙያ ከሌለ ክ/ከተማ ላይ ያለው የራሱ ስራ ድርሻ ላይ ደርቦ ያከናውናል፡፡

14.3. በክ/ከተማ ላይ የተሟላ ባለሙያ ከሌለ በማእከሉ ባለው የራሱ ስራ ድርሻ ላይ ደርቦ ያከናውናል፡፡

**Comment [u16]:** 14.4. ኮሚሽኑ ክ/ከተሞችና ወረዳዎች እንዲሁም ክ/ከተሞች በሥራቸዉ ያሉ የወረዳ ጽ/ቤቶች ይህን ስለመፈጸማቸዉ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋሉ ፤ የሚል ቢጨመርበት

## 15. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ............ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን

መጋቢት/ 2013

አዲስ አበባ